# ማ ር ገ ብ

አጠብቃለሁ ብለህ እንዳትወጥረው
ለመወጠር ስትል እንዳታከረው
ለማክረርም ብለህ እንዳትበጥሰው
መጠኑን ጠብቀህ ረገብ አድርገው
ውጥሩን አላላ የላላውን ወጥር
ማርገብን ዘንግተህ ችግር እንዳትፈጥር

ከሮ እንዳይበጠስ ውጥር ስታላላ
በማርገብ ተጠቀም በዘመኑ መላ
ለማርገብም ብለህ ብዙ እንዳታላላ
መስመሩን ስተኸው ጉድህ እንዳይፈላ
ብዙም ሳይወጠር እጅግም ሳይላላ
በማርገብ ተጠቀም በዘመኑ መላ

የቀድሞው ተማሪ የዛሬው መምህር
ማርገብን ልመደው ውጥር አታክር
የትናንት ውዳቂ የዛሬው ቱጃር
ያለፈውን አስብ ድሆች አታማር
ድሆችን አትጥላ ድሃ ነበርህና
ትዝብትን አታትርፍ ሁሉም ያልፋልና

የትናንቱ ዓይን አፋር የዛሬው ዓይን አውጣ
ጦረኛም ብትሆን ምንም ብትቆጣ
ምክሬን አልነፍግህም እስኪገባህ ድረስ
ጥላቻን አርቀህ ፍቅርህ እስኪመለስ
የትናንቱም ጭፍራ የዛሬው አለቃ
ሕይወት ከዚህ ወዲያ የለም ብለህ በቃ
ተው እንዳትሳሳት ያለፈውን አስብ
ውጥረትን ከመፍጠር ነገሮችን አርግብ

የሚጠቀምህ ቢሆን ምክሬን ይኸው እንካ
በመወጠር ሳይሆን በማርገብ ተመካ
ሀብት ሹመት አለኝ ብለህ አትመካ
ማንም ከማን አያንስ ዕድል ከተሳካ
ነገ እንደ ጥላ በሚያልፍ ሥልጣን
ለሰው ቀምኩ ብለህ ሰውን አትጨቁን
ሰው በወሬ ጠልተህ በወሬ አትውደድ
ጠጋ ብለህ አይተህ ኅሊናህ ይፍረድ

ፊትህን ጨምድደህ ከምትኮሳተር
ሣቅ ፈገግታህ ጠፍቶ ያየህ ከሚቸገር
ጅማትህን አላላው ውጥረቱን አርግበው
ሁሉም አንተን አይቶ ፈገግታን ይጥገበው
ዘመድን ለማብዛት ወዳጅ እንዳታጣ
ፈገግታህ ይትረፍረፍ ፈጽሞ አትቆጣ
ንዴት ቢኖርብህ ብትሆንም ብስጩ
እንዳይደርቅ ተጠንቀቅ የፈገግታህ ምንጩ
በጣም ኮስተር ሳትል ብዙም ሳትለሰልስ
በማርገቡ ዘዴ ፈገግታህን ለግሥ

እንዳትሰለቸኝ ምክሬን ተቀበል
ከድርጊትህ በፊት በጣም አስተውል
ገብጋባ ስስታም ንፉግ ሳትባል
ከዚህ ዓለም ሰው ጋር መኖር እንድትችል
ኪስህ አይቀለፍ በሮቹን አትዝጋ
አለፍ ገደም ስትል እጆችህን ዘርጋ

በጣም ደግ ሰው ነው እንዲሉኝ ብለህ
መጠኑን አትለፍ አስብ ለቤትህ
ድንበሩን እንዳታልፍ የደግነትን
ቸርነት አታብዛ አንዳንደም ጩክን
ክፋትህም ቢሆን እጅጉን ሳይጎላ
ጊዜና ቦታ አይተህ ተጠቀም በመላ
ያለፍህባቸውን ጥምዝምዝ መንገዶች
መከራ ሃዘንን ታላላቀ ችግሮች
ከልብ አስታውሳቸው ዞረህ ወደኋላ
ውጥረትን ለማርገብ እንድታገኝ መላ

ስለ ፍቅርም ቢሆን ሰውን ለመውደድ
በማርገብ ካልያዙት አይቀርም መንደድ
እጅግ ከከረረ ፍቅርም ይበጠሳል
ከደስታውም ይልቅ ሃዘኑ ይብሳል
እጅግ ሳይወጠር በጣምም ሳይላላ
ከተጠቀሙበት በማርገቡ መላ
ሚዛኑን ጠብቆ ማርገብ ከተቻለ
እንደ ፍቅር ጥሩ ምንስ ነገር አለ ?

የላላው ሲወጠር ውጥሩ እንዳይላላ
መፍትሔ ከሆነ የማርገቡ መላ
የዓላማህ መሣሪያ አድርገህ ያዘው
ማርገብን ስትችል ማክረርህ ምነው ?

<u>የግጥሙ ደራሲ መለኮት ባዩህ</u>

<u>መታሰቢያነቱ፤ ሀገር-ፖለቲካ-ነፃነት-የሕዝብ ሰቆቃ ምን ማለት እንደሆነ ላልገባቸው ፤ ፍጥጫ ላይ ለሚ ገኙ የዘር ድርጅትና ለሥልጣነ ጉጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች</u>

የደራሲው መብት የተጠበቀ ነው